*11*

# ለልጆቻቸው ትምህርት ቤት ሲመርጡ ወላጆች መጠየቅ የሚገባቸው 10 ጥያቄዎች


## በከበደ በከሬ

(**ፖ.ሣ.ቁ 121174 አአ፤ ሞባይል 251-911-316756**; Email: trustcounseling@yahoo.com)



**©በከበደ በከሬ፡ ነሐሴ 2002 ዓ.ም.**
**የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው**

Ten Questions Parents Should Ask
to Choose School for Their Children
Copyright ©Kebede Bekere: August 2010
All rights reserved.

***ማስታወሻ፡ ይህን ጽሑፍ በተለያዩ መንገዶች በማባዛት ለሌሎች ሰዎች በነጻ ማስተላለፍ ይፈቀዳል፡፡ ነገር ግን ይህን ጽሑፍ በሙሉም ሆነ በከፊል በተለያዩ መንገዶች በማባዛት ትርፍ ለማግኘት ለሽያጭ ማቅረብ ክልክል ነው፡፡***


የመስከረም ወር ሲቃረብ ወላጆች ስለ ልጆቻቸው ትምህርት ቤት ማሰብ ይጀምራሉ፡፡ ያለፈውን የትምህርት ውጤታቸውን መሠረት በማድረግ ወይም ልጆቻቸው መዋዕለ ሕጻናትን ጨርሰው ወደ አንደኛ ደረጃ ወይም አንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ወደ ሁለተኛ ደረጃ ሲዛወሩ ወይም በሆነ ምክንያት የነበሩበት ትምህርት ቤት ካልተመቻቸው ወላጆች «በሚቀጥለው ዓመት ልጆቼን የት ትምህርት ቤት ላስገባቸው?» ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ወላጆች ቤት ሠርተው ወይም የሥራ ቦታቸውን ቀይረው ሌላ ቦታ  በሚሄዱበት ጊዜ ለልጆቻቸው ትምህርት ቤትን ያፈላልጋሉ፡፡ ወላጆች ለልጆቻቸው የትምህርት ቤት ምርጫ ሲያደርጉ ሊጠይቁ የሚገባቸውን መሠረታዊ ጥያቄዎችን ከመግለጼ በፊት ስለ አንድ ቤተሰብ ታሪክ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ፡፡

በልጅነት ዘመኑ በጥሩ ሁኔታ  ለመማር ዕድል አላገኘም፡፡ አባቱ ከትምህርቱ ይልቅ በእርሻ  እንዲያግዘው ከመፈለጉ የተነሣ ዳንኤል (እውነተኛ ስሙ አይደለም) አጎቱ ወደሚገኝበት ከተማ ሄደ፡፡ አጎቱን እያገለገለ ትምህርቱን በሚገባ ለመማር ተስፋ አደርጎ ነበር፡፡ ሆኖም ከአጎቱ ባለቤት ጋር መስማማት ባለመቻሉ  እዚያም ለትምህርቱ ምቹ ሁኔታ አልተፈጠረለትም፡፡ ባይመቸውም እንደ ምንም አሥራ ሁለተኛ ክፍል መጨረስ ችሏል፡፡ ነገር ግን ወደ ኮሌጅ ሊያስገባው የሚችል ውጤት ማግኘ ት አልቻለም፡፡ ነጥቡ ዝቅተኛ በመሆኑ ተስፋ ቆረጠና የቀን ሥራ ጀመረ፡፡

ለጥቂት ጊዜ አጎቱ ቤት እየኖረ ቀን ሥራውን መሥራት ተያያዘው፡፡ በኋላ ግን ቤት ተከራየና ከእነርሱ ተለይቶ ወጣ፡፡ ከቀን ሥራው ከሚያገኘው ገቢ ለምግቡ፣ ልብስ መግዣና ለቤት ኪራይ ይከፍላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ለተወሰነ ዓመታት ከቆየ በኋላ በዚያ የቀን ሥራ ቦታ የተዋወቃትን አንዲት ወጣት ወደዳት፡፡ እርሷም ወደደችው፡፡ ሁለቱም በራሳቸው ፈቃድ ተጋቡ፡፡ ዳንኤልና ሚስቱ በሦስት ዓመት ውስጥ ሁለት ልጆችን ወለዱ፡፡ ልጆቹ ከተወለዱ በኋላ የዳንኤል ሚስት የቀን ሥራውን በመተው ልጆችን የማሳደግ ኃላፊነት ወሰደች፡፡ ዳንኤል በሚያገኘው የቀን ሥራ ገቢ መተዳደር ቀጠሉ፡፡

ዳንኤልና ሚስቱ ስለ ልጆቻቸው አንድ ነገር ያስባሉ፡፡ ልጆቻቸው ወደፊት የተሻለ ሕይወት እንዲኖራቸው በጥሩ ሁኔታ መማር እንደሚገባቸው ያምናሉ፡፡ ይህም እውን ይሆን ዘንድ ልጆቻቸውን ጥሩ የሚባል ትምህርት ቤት ለማስገባት ወሰኑ፡፡ የልጆቹ ዕድሜ ለትምህርት እንደ ደረሰ ጥሩ የሚባል ትምህርት ቤት የትኛው እንደሆነ በሰፈር የሚያውቁትን ትልልቅ ልጆች ያሉአቸውን ወላጆችን ጠየቁ፡፡ አንዳንዶቹ «እነዚህ የቀን ሠራተኞች ሆነው እንዴት ጥሩ ትምህርት ቤት የትኛው እንደሆነ ይጠይቃሉ ብለው» ያስቡ እንደ ነበር በኋላ ሲያጫውቱአቸው ሰምተዋል፡፡ በእነርሱ አካባቢ ልጆች መልካም ሥነምግባር እንዲኖራቸው የሚሠራና አሥራ ሁለተኛ ክፍል የሚያስፈትናቸው ተማሪዎች ብዙዎቹ

የሚያልፉለት ትምህርት ቤት እንዳለ ይሰማሉ:: ዳንኤል ትኩረት ያደረገው ልጆቹ በእንግሊዘኛ ቋንቋና በሒሳብ ትምህርት የተዋጣላቸው እንዲሆኑ በመሆኑ ትምህርት ቤቱ ከዚህ አንጻር ያለውን ስኬት ጠየቀ:: ምክንያቱም ዳንኤል ኮሌጅ እንዳይገባ መሰናክል የሆነበት አንዱ እርሱ በእንግሊዘኛና በሒሳብ የነበረው ውጤት ነበር። ስለዚህ እነዚህን ሁለቱን የትምህርት ዐይነቶች በልጆቹ ሊበቀል ይፈልጋል። በዚያ ትምህርት ቤት የሚማሩ ልጆች እንግሊዘኛን አቀላጥፈው እንደሚናገሩና በሒሳብም በሌሎች ትምህርት ቤት ከሚማሩ ያላነሱ እንደሆነ ሲሰማ ደስ አለው:: የትምህርት ቤቱ ክፍያ ግን ከፍ ያለ እንደሆነ ባልና ሚስቱ ሰምተዋል::

ዳንኤልና ባለቤቱ የልጆቻቸው የወደፊት ሕይወት መለምለምን እንጂ ለዚህ ሕልም እውን መሆን የሚከፍሉትን መስዋዕትነት በማየት ተስፋ መቁረጥ አልፈለጉም:: ምንም ያህል ሁለቱም ቋሚ የሆነ የገቢ ምንጭ ባይኖራቸው እንዲሁም ከቀን ሥራ የሚያገኙትም ገቢ ከቤት ወጪያቸው ተርፎ ለትምህርት ቤት የልጆች ክፍያ ባይበቃም ልጆቻቸውን የተሻለ ገቢ ያላቸው ወላጆች የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ለማስገባት አቋም ይዘዋል:: ይህን ዓላማቸውን ለጓደኞቻቸው ሲያጫውቱአቸው የደገፉአቸው ጥቂቶቹ ብቻ ነበሩ:: ዳንኤልና ሚስቱ ግን በውሳኔያቸው ጸኑ:: ልጆቻቸውንም ጥሩ የሚባል ትምህርት ቤት አስገብተው እያስተማሩአቸው ይገኛሉ:: «ልጆቻችን ሥራ አጢ ሆነው በኋላ ከምንቸገር አሁን ደህና የሚባል ትምህርት ቤት ገብተው በመማር ጥሩ ውጤት አምጥተው እንዲያልፉ ማድረግ ይሻላል» የሚል የጸና አቋም አላቸው::

ከዳንኤልና ከሚስቱ ውሳኔና እርምጃ እኔ የተማርኩአቸው ቁምነገሮች አሉ:: በመጀመሪያ የኢኮኖሚ አቅማቸው ዝቅተኛ ቢሆንም የልጆቻቸው የወደፊት ሕይወት ከእነርሱ ኑሮ የተሻለ እንዲሆን ለማድረግ ልጆቹ በትምህርታቸው ስኬታማ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሆነ ያላቸውን ግንዛቤ አደንቃለሁ:: ትምህርት የስኬት ቁልፍ መሆኑ ገብቶአቸዋል:: በመቀጠልም ዳንኤልና ሚስቱ ልጆቻቸውን የሚልኩበት ትምህርት ቤት የትኛው እንደሆነ ለማወቅ ይህን ጉዳይ ያውቃሉ ብለው ያሰቡትን ሌሎች ወላጆችን መጠየቃቸው የሚደገፍ ነው:: በትምህርት ላይ ያሉ ልጆች ያሉአቸው ወላጆች ልጆቻቸው ስለሚማሩበት ትምህርት ቤት መረጃ ይኖራቸዋል:: ስለዚህ በዚህ ነገር ምክር መፈለጋቸው በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ እንዲያደርጉ ከማገዝ አንጻር የሚኖረው ሚና ከፍ ያለ ነው:: በሦስተኛ ደረጃ ጥሩ ትምህርት ቤት ለመምረጥ የተጠቀሙባቸው መስፈርቶችም ተቀባይነት ያላቸው ናቸው:: ትምህርት ቤቱ ልጆችን በሥነምግባር ለማሳደግ ጥረት ማድረጉና ብዙ ተማሪዎች 12ኛ ክፍል በበቂ ውጤት ማለፍ መቻላቸው ትምህርት ቤቱን እንዲመርጡ አድርጓል::

በሌላ በኩል ግን ዳንኤልና ባለቤቱ የወሰዱት እርምጃ ደካማ ጎን ያለው እንደሆነም አስባለሁ:: ወላጆች ልጆቻቸውን ለማስተማር የሚቻላቸውን ዋጋ



መክፈል እንደሚገባቸው አምናለሁ:: ይህ እንዳለ ሆኖ ቤተሰቡ በኢኮኖሚ ሳይጎሳቆል ወይም ሁልጊዜ ስለ ልጆች የትምህርት ቤት ክፍያ እያሰበ በጭንቀት ከመኖር ሌላ አማራጭ መንገድ መፈለግ ቢቻልስ ብዬ አስባለሁ:: «ልጆች ከፍተኛ ክፍያ የሚጠይቅ ትምህርት ቤት ገብተው ከተማሩ በትምህርታቸው ውጤታማ ይሆናሉ» የሚለው እሳቤ ምን ያህል እውነት እንደሆነ መፈተሽ የሚያስፈልግ እመስለኛል:: ልጆች የሚማሩበት ትምህርት ቤት ጥራት ብቻውን ልጆች በትምህርታቸው ስኬታማ እንዲሆኑ አያደርግም::

የዳንኤል ትኩረት ልጆቹ እንግሊዘኛ ቋንቋን በደንብ እንዲለምዱለትም ጭምር ነው:: በእርግጥ ልጆች የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ሲኖራቸው ራሳቸውን በቋንቋው መግለጽ ከመቻልም ባሻገር ሌሎች ትምህርቶችን በሚገባ ለመሥራት ይጠቅማቸዋል:: የዳንኤል ትኩረት ከዚህ አንጻር የሚደገፍ ነው:: አንድ ተማሪ በሌሎች ትምህርቶች አጥጋቢ ውጤት አምጥቶ በእንግሊዘኛና በሒሳብ ከወደቀ ኮሌጅ የመግባት ዕድል የለውም:: ስለዚህ ወላጆች በእነዚህ ሁለቱ የትምህርት ዐይነቶች ጥሩ ትምህርት የሚሰጡትን ትምህርት ቤቶች መምረጣቸው የሚደገፍ ነው::

ልጆች እንግሊዘኛ ቋንቋን መናገር መቻላቸው ግን እንግሊዘኛን ቻሉ ማለት ላይሆን ይችላል:: አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ልጆችን ከመዋዕለ ሕጻናት ጀምረው እንግሊዘኛ ንግግርን ያስለጥኑአቸዋል:: ልጆቹም በእንግሊዘኛ መናገርን ይለምዳሉ:: ቤተሰብ ልጆቹ በእንግሊዘኛ መናገራቸውን ሲያይ ትምህርት ቤቱን ማድነቅ ይጀምራል:: ትምህርት ቤቱ ክፍያ ቢጨምርም ዋጋ ክፍለው ለማስተማር ይወስናሉ:: ወላጆች መገንዘብ ያለባቸው ልጆች የእንግሊዘኛ ችሎታ ንግግር መቻላቸው አንድ ጥሩ ጅምር እንጂ በሁሉም ትምህርት ውጤታማ መሆናቸውን እንደማያሳይ ነው:: እንግሊዘኛውንም ንግግሩን፣ ጽሑፉንና ንባቡን በደንብ መቻላቸው መታወቅ አለበት::

> **ለልጆቹ ትምህርት ቤትን የሚመርጡ ወላጆች ናቸው**

ለልጆች ትምህርት ቤትን መምረጥ ያለበት ወላጆች ናቸው:: ምክንያቱም ከወላጆች በላይ ለልጆቹ የሚያስብ አካል ስለሌለ ነው:: ወላጆች ለልጆቻቸው ትምህርት ቤት በሚመርጡበት ጊዜ ሦስት ነገሮችን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል:: እነርሱም የልጆቻቸውን ሁኔታ ማወቅ፣ የትምህርት ቤቱን አጠቃላይና ዝርዝር ገጽታ መገንዘብና የቤተሰብ እሴትንና የኢኮኖሚ አቅምን ማወቅ ናቸው::

ጠንቃቃ ወላጆች የልጆቻቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን፣ ባሕርይና ፍላጎት ስለሚያውቁ የት ትምህርት ቤት ቢገቡ በትምህርታቸው ስኬታማ ሊሆኑ

እንደሚችሉና በመልካም ሥነምግባር ታንጸው እንደሚያድጉ ይገነዘባሉ:: ስለዚህ ለልጆች የሚመጥናቸውን ትምህርት ቤት ለመምረጥ በቅድሚያ ወላጆች ስለ ልጆቻቸው ሁኔታ ማወቅ አለባቸው:: በተለይ ልጆቹ ምን ይፈልጋሉ? የሚለውን ጥያቄ ብስለት ባለው መንገድ መመለስ ለምርጫው ያግዛቸዋል::

ወላጆች ስለ ልጆቻቸው ማወቅ ከሚገባቸው ነጥቦች መካከል ጥቂቶቹ: ልጆቹ በግል ብዙ ትኩረት ይፈልጋሉ ወይ? አንድን ነገር በግላቸው መሥራት ይችላሉ ወይስ የአዋቂን ድጋፍ በብዛት ይፈልጋሉ? የሒሳብና የቋንቋ ችሎታቸው ምን ያህል ነው? ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆኑ ተጨማሪ እገዛ ያስፈልጋቸዋልን? የሚሰጣቸውን የቤት ሥራ በተመጣጣኝ ጊዜ ይጨርሳሉ ወይስ ክትትል ይፈልጋሉ? የተለየ ተሰጥኦ አላቸው? ከአካል ጉዳተኝነት የተነሣ የተለየ የማስተማር ስልትን ይፈልጋሉ? የሚሉና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በማንሳት ወላጆች መልስ ካገኙላቸው ከዚህ አንጻር ትምህርት ቤት መፈለግ ይችላሉ:: ልጆች ወደፊት መሆን የሚፈልጉትን/የሚችሉትን ለመሆን ተገቢውን ትምህርት መማር አለባቸው:: ለዚህ ደግሞ ወላጆች ትምህርት ቤትን ለልጆቻቸው ሲመርጡላቸው በተገቢው መረጃ ላይ የተመረኮዘ ምርጫ ማድረግ አለባቸው::

በገጠርቷ የሀገራችን ክፍል ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ለመላክ ከፈለጉ የትምህርት ቤት ምርጫ ስለማድረግ እምብዛም አይጨነቁም:: ምክንያቱም ብዙ ትምህርት ቤቶች በቅርብ ርቀት ባለመኖራቸው ነው:: በአብዛኛው እንደ ዋነኛ መሥፈርት የሚወሰደው ርቀቱና መንገዱ ለልጆች ዋስትና ያለው መሆኑ ነው:: ወንዝ ወይም በልጆች ላይ ጥቃት ሊያደርስ የሚችል ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ ትምህርት ቤት ለመምረጥ በቂ ነው:: በከተማ አካባቢ ግን ብዙ ትምህርት ቤቶች በመኖራቸው ምክንያት ወላጆች ልጆቻቸውን የት ትምህርት ቤት ማስገባት እንደሚገባቸው መምረጥ ይገባቸዋል:: ወላጆች ለልጆቻቸው ትምህርት ቤት ሲመርጡ በአካባቢያቸው ያሉ ትምህርት ቤቶችን በማሰስ መረጃ ማግኘት ጠቃሚ ነው::

ለልጆች ትምህርት ቤትን ለመምረጥ የመጀመሪያው እርምጃ ስለ ትምህርት ቤቶች መረጃ መሰብሰብ ነው:: ትምህርት ቤቶች የተለያየ ደረጃ አላቸው:: ስለተለያዩ ትምህርት ቤቶች መረጃን ለማግኘት ጓደኞችን፣ ጎረቤትንና መምህራንን መጠየቅ ይቻላል:: በዐውዳችን አልፎ አልፎ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች በተለያዩ የመገናኛ ብዙኋን ማስታወቂያ ስለሚናገሩ ያንን በመከታተል መረጃ ማግኘት ይቻላል:: በክፍለ ከተማ ደረጃ ያለው የትምህርት ክፍልም በክፍለ ከተማው ውስጥ ስለሚገኙ ትምህርት ቤቶች መረጃ ሊሰጥ ይችላል::

**ወላጆች ስለ ትምህርት ቤቶች መረጃ ከየት ያገኛሉ?**



ጥቂት ትምህርት ቤቶችን በመምረጥ በአካል ሄዶ ትምህርት ቤቶቹን ማየት ጠቃሚ ነው:: እንደ አስፈላጊነቱ ከትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ጋር ቀጠሮ በመያዝ ማነጋገር የሚፈለገውን መረጃ ለማግኘት ያግዛል:: ይህ በማይቻልበት ሁኔታ ደግሞ በትምህርት ቤቱ የወላጅ ቀን ስብሰባ ላይ መገኘት ነው:: በዚህ ዕለት ትምህርት ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፣ ወላጆች ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ ወይም አስተያየት ይሰጣሉ፣ የትምህርት ቤቱ አመራር ለጥያቄዎቹና ለአስተያየቶች ምላሽ ይሰጣል:: ከእነዚህ ነገሮች በመነሳት የትምህርት ቤቱን ማሕበረሰብና የወላጆችን አስተሳሰብና አመለካከት በአጭሩ መገንዘብ ይቻላል::

ወላጆች ወደ ትምህርት ቤት በመምጣት ትምህርት ቤቱን በማየት፣ ከአንዳንድ የትምህርት ቤቱ ማሕበረሰብ ጋር በመነጋገር፣ ጎረቤትን ወይም ጓደኛን በመጠየቅ ስለ አንድ ትምህርት ቤት ብዙ ነገሮችን መረዳት ይችላሉ:: ከዚህም ያገኙትን መረጃ በመጠቀም ስለ ትምህርት ቤቱ ሁኔታ ይገመግማሉ:: ልጆቻቸውን ወደዚያ ትምህርት ቤት ለመላክ ወይም ላለመላክም ይወስናሉ::[1]

## ለልጄ የቱ ይሻላል?




በአጠቃላይ የመንግሥት፣ የሕዝብና የግል ትምህርት ቤቶች ይኖራሉ:: ከባለቤትነት አንጻር በመመልከት የትምህርት ቤቶችን ጥራት መለካት አዳጋች በመሆኑ ሌሎች መሥፈርቶችን መጠቀም የተሻለ ይሆናል:: የመንግሥት ከሕዝብ ወይም የሕዝብ ከመንግሥት ወይም የግል

[1] Glasgow, Neal A. & Whitney, Paula J. *What Successful Schools Do To Involve Families: 55 partnership Strategies.* Corwin Press, 2009. P. 3

ከመንግሥት ወይም የመንግሥት ከግል ትምህርት ቤት የተሻለ ነው ብሎ መደምደም ተገቢ አይደለም፡፡

ወላጆች ልጆቻቸውን የት ትምህርት ቤት ማስገባት ወይም ማቆየት እንደሚፈልጉ ሲያስቡ እንደ መስፈርት ሊጠቀሙባቸው የሚገቧቸው መሠረታዊ ሐሳቦች አሉ፡፡ የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ የትምህርት ቤት ግምገማ መሥፈርት ማስቀመጥ ወይም በዐውዳችን ያሉ ትምህርት ቤቶች እንዲህ ወይም እንዲያ ናቸው ብሎ አስተያየት መስጠት አይደለም፡፡ ይህ ሐሳብ ከዚህ ጽሑፍ በላይ ነው፡፡ ዋና ዓላማው ወላጆች ለልጆቻቸው ትምህርት ቤት በሚመርጡበት ጊዜ ማየት ከሚገቧቸው ነጥቦች መካከል ዋና ዋና የሚባሉትን ነጥቦች ለማብራራትና ወላጆች በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ እንዲያደርጉ ለማገዝ ነው፡፡

## *ወላጆች ለልጆቻቸው ትምህርት ቤትን ሲመርጡ መጠየቅ የሚገቧቸው ጥያቄዎች*

ወላጆች ለልጆቻቸው ተገቢውን ትምህርት ቤት ለመምረጥ ጠቃሚ መረጃዎችን ማግኘት ይገባቸዋል፡፡ ትምህርት ቤቱ እነርሱ ለልጆቻቸው የሚፈልጉትን ዐይነት ትምህርት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ መስጠቱን ለማወቅ ደግሞ ተገቢ ጥያቄዎችን መጠየቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ስለ አንድ ትምህርት ቤት ጥሩነት ወይም *ስኬታማነት*[2] ወላጆች ማወቅ የሚገባቸውን መረጃ ለማግኘት የሚያግዙአቸው ዋና ዋና ጥያቄዎች ከዚህ በታች ተጠቅሰዋል፡፡

**1. የትምህርት ቤቱ አመራር ብቃት አለውን?**

የአንድ ትምህርት ቤት ስኬታማነትን ከሚያሳዩ ምልክቶች መካከል አንዱ የትምህርት ቤቱ አመራር ብቃት ያለው መሆኑን ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ ራእይ፣ ስልታዊ ዕቅድና ለዚህም ተግባራዊነት የተሰጠ አመራር ካለው የትምህርቱን ጥራት በመጠበቅ ተማሪዎቹን ማሳደግ ይችላል፡፡ አመራሩ ብቃት ሲኖረው አንድ ዐይነት አሠራር ብቻ ይዞ ከመኖር ይልቅ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር አብሮ የሚሄድ ስልት በመቀየስ ተማሪዎቹ በትምህርታቸው ስኬታማ እንዲሆኑ በትጋት ይሠራል፡፡

[2] በዚህ ጽሑፍ ውስጥ *ስኬታማ* የሚለው ሐሳብ ትምህርት ቤቱ የያዘውን ተማሪዎች በተከታታይነት ከፍተኛ ውጤት እንዲያገኙ ማድረግ መቻሉንና የተማሪዎቹ የትምህርት ውጤት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄድን ማሳየቱን ያመለክታል



የትምህርት ቤቱ አመራር በሥራ ትጋትና በሥነምግባር ለትምህርት ቤቱ ማሕበረሰብ አርዓያ የሚሆን፤ አሳታፊ አመራር የሚከተል፣ አንድነት በልዩነት መርህን የሚተገብር፣ በመምህራን አቅም ግንባታ ላይ ትኩረት የሚሰጥና ራሱን እየገመገመ ለውጥ የሚያደርግ ሲሆን ስኬታማ ትምህርት ቤት ነው ማለት ይቻላል፡፡

**2. በአንድ ክፍል ስንት ተማሪዎች ይማራሉ?**

ተማሪዎች ተገቢውን ትምህርት ማግኘት የሚችሉት ትምህርቱን የሚያስተምሩ መምህራን ከእያንዳንዱ ተማሪ ጋር ተገቢውን ግንኙነት ሲያደርጉ ነው፡፡ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ማወቅ የሚችሉት በአንድ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር መጠነኛ ሲሆን ነው፡፡ በአንድ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ብዙ ከሆኑ መምህራን ከእያንዳንዱ ተማሪ ጋር መቀራረብ አይችሉም፡፡ የተማሪዎች ችሎታ፣ ፍላጎት፣ ተግዳሮት ወይም ችግር ምን እንደሆነ በማወቅ ተገቢውን ክትትል ማድረግ አይችሉም፡፡ ስለዚህ የመምህራን ተማሪዎች ጥምርታ አነስተኛ መሆን አለበት፡፡በሀገራችን በአንድ ክፍል ውስጥ መማር ያለባቸው የተማሪዎች ቁጥር ሃምሳ ነው፡፡ ይህ ከፍተኛ ጣሪያው ነው፡፡

ወላጆች ስለ ትምህርት ቤት ጥናት በሚያደርጉበት ጊዜ የመምህራን ተማሪዎች ጥምርታ ምን ያህል እንደሆነ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ የትምህርት ቤቱን አስተዳደር ወይም መምህራንን በመጠየቅ ማወቅ ይቻላል፡፡ በዚያ ትምህርት ቤት የሚማሩትንም ተማሪዎች በመጠየቅ መረጃ ማግኘት ይቻላል፡፡ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያለው ጥምርታ አንድ መምህር ለ15 ተማሪዎች ሲሆን መምህሩ ከእያንዳንዱ ተማሪ ጋር ግንኙነት ማድረግ አይከብድም፡፡[3] በአንድ ክፍል 15 ተማሪን ማስተማር በዐውዳችን የማይታሰብ ስለሚሆን አንድ ወይም ሁለት ረዳት መምህር በማስማራት ችግሩ በመጠኑም ቢሆን ይቀረፋል፡፡ ስለዚህ ወላጆች ዋና መምህርና ረዳት መምህራን አብረው አንድ ክፍል ውስጥ ማስተማራቸውንም ጠይቆ መረዳት ይችላሉ፡፡

በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች በአብዛኛው በተመሳሳይ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ ሁሉም በተመሳሳይ መልኩ የመምህራቸውን ትኩረትና እገዛ ይሻሉ፡፡ ይህ ማለት ግን ሁሉም ተማሪ ተመሳሳይ ነው ማለት አይደለም፡፡ የእያንዳንዱ ተማሪ የትምህርት አቀባበል ሁኔታ ይለያያል፡፡ ችሎታ ብቻም ሳይሆን የፍላጎት ልዩነትም ይኖራል፡፡ እነዚህ ልዩነቶች ደግሞ መምህሩ ለእያንዳንዱ ተማሪ እንደ ችሎታው፣

[3] Gurrian, Michael, et al. *Boys and Girls Learn Differently: A Guide for Teachers and Parents.* 2001. P. 130

ፍላጎቱና ችግሩ ምላሽ እንዲሰጥ የሚጠይቁ ናቸው:: መምህራን በትምህርት አቀባባል ፈጣን ያልሆኑትን በግል የሚያግዙአቸው ሲሆንና አስፈላጊውን ምክር የሚሰጡ ከሆነ ጥሩ ትምህርት ቤት ነው::

መምህራንና የትምህርት ቤቱ አመራር ከተማሪዎቻቸው ጋር ግንኙነት በመፍጠር ተማሪዎቻቸውን በቅርበት የሚያውቁአቸው ሲሆን ለእያንዳንዱ ተማሪ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት ያደርጋሉ:: እያንዳንዱ ተማሪ በግል የሚታወቅ ሲሆን በዚያ ትምህርት ቤት ውስጥ ለመቆየትና ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ ጥረት እንደሚያደርጉ ፍንጭ ይሰጣል::

### 3.ትምህርት ቤቱ የተማሪዎችን ሥነ ምግባር ለማነጽ ምን ያህል ይሠራል?

ተማሪዎች የቀለም ትምህርት ብቻ ሳይሆን በሥነምግባርም የታነጹ ዜጎች መሆን አለባቸው:: አንድ ትምህርት ቤት ጥሩ ነው የሚባለው ተማሪዎቹ በቀለም ትምህርት ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው መሆናቸውና ውጤት ማምጣታቸው ብቻ አይደለም:: ይህ እንዳለ ሆኖ ተማሪዎቹ በሥነምግባርም የታነጹ ሆነው ችሎታቸውን ለገንቢ ነገር በዘላቂነት መጠቀም የሚችሉበት ሁኔታ እንዲፈጠር ሲደረግ ነው::

ለሥነምግባር ግንባታ ትኩረት መስጠታቸውን ከሚያመላክቱ ነገሮች አንዱ ለተማሪዎች ያዘጋጁት የሥነሥርዓት ደንቦች ናቸው:: አንድ ተማሪ እነዚህን ትምህርት ቤቱ እንደ ደንብ ያስቀመጣቸውን ነገሮች ጥሶ ቢገኝ ምን ዐይነት እርምጃ ይወሰድበታል? ከዚህ አንጻር የትምህርት ቤቱን ሥርዓት ባላከበሩት ላይ የወሰዳቸውን እርምጃዎች በመጠየቅ መረጃ ማግኘት ይቻላል:: የዲስፕሊን እርምጃ መውሰድ ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች በሥነምግባር የታነፁ እንዲሆኑ ለማድረግ የሥነልቦና የምክር አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያ መኖሩንም መጠየቅ ተገቢ ነው::

አንድ ጊዜ በትምህርት ዓመቱ ማጠቃለያ የወላጆች ጉባኤ ላይ ተገኝቼ ነበር:: ርዕሰ መምህሩ ስለ ትምህርት ቤቱ ሪፖርት ካቀረቡ በኋላ ከወላጆች መካከል አንዱ ቅሬታ አቀረቡ:: ቅሬታቸውም በዚያ ትምህርት ቤት ውስጥ ከሚማሩ ልጆቹ መካከል አንዱ የደረጃ ተማሪ ሆኖ እያለ ከትምህርት ቤቱ በዲስፕሊን ምክንያቱ መባረሩ ተገቢ አለመሆኑን የሚገልጽ ነበር:: የገረመኝ የርዕሰ መምህሩ ምላሽ ነበር:: «የእኛ ትኩረት ብሩዕ አእምሮ ያላቸውንና በመልካም ሥነምግባር የታነፁ ዜጎችን መፍጠር ነው» በማለት የአእምሮ ችሎታ መልካም ሥነምግባር በሌለበት ዐውድ ለግለሰቡም ሆነ ለኅብረተሰቡ እንደማይጠቅም መናገራቸው ነው::

በእርግጥ የአእምሮ ችሎታ ብቻውን ዋጋ የለውም:: ልጆች በሥነምግባር ታንጸው ማደግ አለባቸው:: ለዚህ ደግሞ ትምህርት ቤት



ልጆች ብዙውን ጊዜአቸውን የሚያሳልፉበት ሥፍራ በመሆኑ ከፍተኛ ሚና አለው::

ትምህርት ቤቱ ለሥነምግባር ግንባታ አትኩሮት መስጠቱን ለማመልከት ከሚያደርጋቸው ነገሮች መካከል አንዱ በሥነምግባር አርዓያ የሆኑ ተማሪዎችን በየጊዜው መሸለም ነው:: ተማሪዎች ለመልካም ሥነምግባራቸው መሸለማቸው ሰናይ ምግባር እንደሚፈለግና ብድራትም እንዳለው እንዲገነዘቡ ዕድል ይሰጣቸዋል::

በብዙ ትምህርት ቤቶች በትምህርት ዓመት መጨረሻ ላይ የደረጃ ተማሪዎች ይሸለማሉ:: እነዚህ ተማሪዎች ከወላጆች ቀን ሁለት ወይም ሦስት ቀን በፊት እንዲመጡ በስልክ ይነገራቸዋል:: ለእኔም ልጅ ተደወለላትና አብረን ሄድን:: በትምህርት ባላቸው የክፍል ደረጃና አጠቃላይ ሽልማት ተሰጣቸው:: ይህ የትምህርት ደረጃ የሽልማት ሥነሥርዓቱ ሲያልቅ ሌላም ሽልማት ቀጠለ::

አንደኛና ሁለተኛ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን በመወከል ሁለት ተማሪዎች በመልካም ሥነምግባራቸው እንደሚሸለሙ ተነገረ:: ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተጀመረ:: «ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘንድሮ የመልካም ፀባይ ተሸላሚ ርሆቦት ከበደ!» ብሎ ጠራ:: ርሆቦት ወደ መድረክ ስትወጣ ርዕሰ መምህሩ «ርሆቦት በክፍሏ በትምህርት ዝቅተኛ ውጤት ያላቸውን ተማሪዎች በመሰብሰብ መምህር ከክፍል በሚቀርበትና በዕረፍት ሰዓት በማስተማር ውጤታቸውን እንዲያሻሽሉ በማድረጓ የዚህ ዓመት የአንደኛ ደረጃ የሥነምግባር ኮከብ ናት» በማለት ምሥክርነት ሲሰጥ እኔ የሰማሁትን ማመን አቃተኝ:: በትምህርት ካገኘችው ደረጃ ይልቅ ይህኛው ሐሴት እንዳደረግ አደረገኝ:: ከአዳራሹ ስንወጣ አንዳንድ ወላጆች «አንቺ በሁሉም ነገር ጎበዝ ነሽ» እያሉ እጅዋን እየጨበጡ «በርቺ» ይሏት ነበር::

ተማሪዎች በሥነምግባር የታነጹ እንዲሆኑ ጥረት የሚያደርግ ትምህርት ቤት ልጆች እርስ በርስ መከባበርን፣ ታማኝነትን፣ ግልጽነትን፣ ኃላፊነት መሸከምን፣ ተገቢ ድፍረትንና ሌሎችም ጠቃሚ እሴቶችን እንዲለማመዱ ዕድል ይሰጣቸዋል:: አንዳንድ ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጭ የሚያሳዩትን ባሕርይ በመመልከት ከየት ትምህርት ቤት እንደመጡ መገመት ይቻላል::

በአብዛኛው በዐውዳችን ተማሪዎች መምህራንን እንደ ዕውቀት አባት ስለሚያስቡ ያከብሩአቸዋል:: ከዚህም በላይ በዕድሜ የገፉትን እንደ ወላጆቻቸውና ወጣቶቹን ደግሞ እንደ ታላቅ ወንድምና እህታቸው ስለሚያዩአቸው መምህራን ወሰናቸውን ጠብቀው በአክብሮት ሲመላለሱ ተማሪዎች ሥነሥርዓት ይጠብቃሉ:: አልፎ አልፎ አንዳንድ መምህራን ስድብ የተቀላቀለ ምክር ሲመክሩአቸው እንኳ ተማሪዎች ለመቀበል

ፈቃደኞች እንደሆኑ ይገልጻሉ::[4] ይህ ማለት መምህራን ተማሪዎቻቸውን ሲወዱና ሲያከብሩ ተማሪዎችም እንደሚወዱአቸውና እንደሚያከብሩአቸው ያሳያል ብዬ አስባለሁ::

በትምህርት ቤቶች ውስጥ መምህራን ልጆችን በአርጩሜ መምታት አይፈቀድላቸውም:: ልጆች በሚያጠፉበት ጊዜ መምከርና አስፈላጊ ከሆነ ወላጅ እንዲጠሩ ማድረግ እንጂ በዱላ መምታት የልጆችን ሰብዓዊ መብት መጣስ ነው:: የልጆች ሰብዓዊ መብት የሚከበርበት ትምህርት ቤት ለልጆች ደህንነት ዋስትና አለው:: ወላጆች ልጆቻቸው ላይ ጥቃት እንደማይደርስ ያምናሉ፤ ልጆችም ያለ ስጋት ይማራሉ:: መምህራን ተማሪዎቻቸውን በማክበር አክብሮትን የሚያገኙበት ትምህርት ቤት ተመራጭ ነው::

ስለዚህ ወላጆች ትምህርት ቤቱ ልጆች በሚያጠፉበት ጊዜ የሚጠቀሙባቸውን የሥነ ሥርዓት እርምጃዎችን መጠየቅ አለባቸው:: መምህራን ልጆችን በዱላ የሚመቱ ከሆነ ልጆችን ወደዚያ ትምህርት ቤት መላክ አይመከርም:: አንዳንድ ጊዜ መምህራን ልጆችን በዱላ ባይመቱም ተገቢ ያልሆኑ ቃላትን በመጠቀም ልጆችን ሊሳደቡና ስብዕናቸውን በሚያዋርድ መልክ ሊናገሩአቸው ይችላሉ:: አንዳንዱ ቃላት ከዱላ የባሰ ይጎዳሉ:: ዱላ ውጫዊ አካልን ሲጎዳ ተገቢ ያልሆኑ ቃላት ግን ውስጣዊ ማንነትን ያቆስላሉ:: መምህራን ልጆችን ሲሳደቡ ወይም በአርጩሜ ሲገርፉ ወይም ተገቢ ያልሆነ ባሕርይ ሲያሳዩአቸው የትምህርት ቤቱ አመራር ምንም እርምጃ የማይወሰድባቸው ከሆነ ልጆችን እዚያ ትምህርት ቤት ማስገባት አይመከርም::

## 4. ትምህርት ቤቱ ከተማሪዎቹ ከፍተኛ ውጤት ይጠብቃልን?

የልጆች የትምህርት ውጤት ትምህርት ቤቱ ከእነርሱ በሚጠብቀው ልክ ይሆናል:: መምህራን ከተማሪዎቻቸው ከፍተኛ ውጤት የሚጠብቁና ወደዚያም እንዲደርሱ አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያደርጉ ሲሆን የተማሪዎች ውጤት ከፍተኛ ይሆናል:: ስለዚህ ተማሪዎቹ ከክፍል ወደ ክፍል እንዲዛወሩ ብቻ ሳይሆን በሀገርቷ ውስጥ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ልቆ ለመገኘት ተማሪዎቹን የሚያተጋ ትምህርት ቤት ተማሪዎቹ ያላቸውን የትምህርት እምቅ ችሎታ ፈልቅቀው እንዲያወጡ ዕድል ይሰጣቸዋል:: ጤናማ የሆነ የውድድር መንፈስ በትምህርት ቤቱ ማሕበረሰብ ውስጥ በሚኖርበት ጊዜ ተማሪዎቹ ራሳቸውን ከታወቁ ትምህርት ቤቶች ጋር ማወዳደርና ከእነርሱ በልጦ ለመገኘት ይሠራሉ::

[4] Poluha, Eva. *The Power of Continuity: Ethiopia through the eyes of its children.* The Nordic Africa Institute. Stockholm, 2004, p. 116



ተማሪዎች በትምህርታቸው ከሌሎች መጥቀው እንዲገኙ መጠበቅ ሲባል እያንዳንዱ ተማሪ ራሱን ማወዳደር ያለበት በትምህርት ቤቱ ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች ጋር ሳይሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተቀመጠው መለኪያ አንጻር ነው:: ሁሉም ተማሪ ሊያመጣው የሚገባው ዝቅተኛ ነጥብ ከወዲሁ ታውቆ ሁሉም ከዚያ በላይ እንዲያመጣ መጠበቅ ሁሉም ተማሪዎች በትጋት እንዲሠሩ ያደፋፍራል:: በእርግጥ ከሚጠበቀው ውጤት በታች የሚያመጣ ተማሪ በዚያ ትምህርት ቤት ውስጥ መቀጠል እንደማይችል ከወዲሁ ያውቃል::

እያንዳንዱ መምህር ከሚያስተምረው ትምህርት አንጻር ከተማሪዎቹ የሚጠብቀውን ውጤት በግልጽ በማሳወቅ ያንን ማምጣት እንዲችሉ አስፈላጊውን እገዛ በሚያደርግበት ጊዜ ተማሪዎቹ በትምህርታቸው ይመጥቃሉ:: ተማሪዎቹም ብዙ ሰዓታቸውን በትምህርት ላይ ማሳለፍ ይጠበቅባቸዋል:: ከክፍል ውጭ ባሉት ሰዓታት የቤት ሥራዎችን ለመሥራትና ተጨማሪ መጻሕፍትን ለማንበብ ራሳቸውን መስጠትና ሥርዓት ያለው የሕይወት ዘይቤ ያስፈልጋቸዋል::

በአጠቃላይ ትምህርት ቤቱ በቅርበት ደግሞ እያንዳንዱ መምህር ከተማሪዎቹ የሚጠብቀውን ውጤት ሲያሳውቃቸው ተማሪዎች ሊደናገጡ ይችላሉ:: ነገር ግን ከተማሪዎች ከፍ ያለ ውጤት መጠበቅ ማለት መምህራን ትጉ ሠራተኞችና ጎበዞች መሆናቸውንና መምህራን በተማሪዎቻቸው እምቅ የትምህርት ችሎታ እምነት እንዳላቸው መልዕክት ያስተላልፋል:: ስለሆነም ከሚጠበቅባቸው መለኪያ በታች ላለመገኘት እያንዳንዱ ተማሪ ከራሱ ጋር ቃል እንዲገባ ዕድል ይሰጠዋል:: ብዙ መምህራን ተማሪዎቹ ተስፋ እንዳይቆርጡ በቃልና በጽሑፍ ዓመቱን በሙሉ ያበረታቱአቸዋል:: እያንዳንዱን የትምህርታቸውን ምዕራፍ ሲጨርሱ ተማሪዎቹ በትክክል መገንዘባቸውንና ከሚጠበቀው ውጤት በላይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ፈተና ይሰጡአቸዋል:: ይህ ተማሪዎቹ በእያንዳንዱ ምዕራፍ ከሚጠበቀው ውጤት በላይ በማምጣት በራስ የመተማመን ስሜት እንዲኖራቸውና ወደፊትም በዚሁ እንዲቀጥሉ ያደርጋቸዋል::[5] ይህን ስልት በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ መጨረሻ ላይ ተማሪዎቹ ምን ያህል እንደ ተገነዘቡ ለመረዳትም ይረዳል::

ስለዚህ ወላጆች ለልጆቻቸው መምረጥ ያለባቸው ትምህርት ቤት ልጆቻቸውን የሚያዝናና ሳይሆን ብዙ ሰዓት የሚያሠራቸውን ነው:: የተማሪዎቹ ውጤትና እምቅ ችሎታቸውን የመጠቀማቸው ሁኔታ

[5] ይህ አቀራረብ በFred Keller ከተጀመረው PSI (Personalized System of Instruction) ከሚባል የማስተማር ስልት የተወሰደ ሲሆን ስኬታማነቱ በብዙ ጥናቶች እንደ ተረጋገጠ አንብቤአለሁ::

ከትምህርት ቤቱ በሚጠበቅባቸው መጠን ስለሚሆን ትኩረት ሊደረግበት እንደሚገባ አምናለሁ፡፡

### 5. መምህራን ለተማሪዎች ተከታታይነት ያለው ክትትልና ግምገማ ያደርጋሉ ወይ?

መምህራን የተማሪዎቻቸውን ሥራ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ የሚከታተሉና በየጊዜው ተማሪዎች ትምህርቱን ምን ያህል እንደ ተገነዘቡ ግምገማ የሚሰጣቸው ሲሆን የተማሪዎች ውጤት ጥሩ ይሆናል፡፡ አንድ መምህር የቤት ሥራ የሚሰጥና እያንዳንዱ ተማሪ የቤት ሥራውን መሥራቱን የሚከታተልና ለተሠራው ሥራ ነጥብ የሚሰጥ ሲሆን ተማሪዎች የቤት ሥራውን በሚገባ ይሠሩታል፡፡ የቤት ሥራ የማይታረም ከሆነ ግን ተማሪዎች ላይሠሩት ይችላሉ፡፡

ይህን ለማወቅ የዚያን ትምህርት ቤት ተማሪ ደብተር ማየት ብዙ መረጃ ይሰጣል፡፡ መምህሩ በተማሪው ደብተር ላይ በየጊዜው ምልክት/ ፊርማ/ የሚያደርግ ከሆነ ክትትል መኖሩን ያሳያል፡፡ እነዚህ የሚሰጡ የቤት ሥራዎችም ከትምህርት ይዘቱ ጋር ቀጥተኛ ተዛማጅነት ያላቸውና የተማሪዎችን አእምሮ የሚያሠሩ ናቸው፡፡ ከዚህ የተነሣ ተማሪዎች አብዛኛ ውን ጊዜአቸውን በትምህርት ላይ (ክፍል ውስጥ በመማር፣ የቤት ሥራ በመሥራት፣ በማንበብና በማጥናት) የሚያሳልፉ ከሆነ ሠርቶ ተማሪዎችን የሚያሠራ ትምህርት ቤት በመሆኑ ተመራጭ ይሆናል፡፡

### 6. መምህራን ክፍለ ጊዜያቸውን ለትምህርት ምን ያህል ይጠቀማሉ?

አንዳንድ መምህራን ክፍል በሚገቡበት ጊዜ የሚያስተምሩትን የትምህርት ዐይነት በሚገባ ከማስተማር ይልቅ ከተማሪዎች ጋር የተለያዩ ጉዳዮችን እያነሱ ያወራሉ፡፡ የትምህርት ክፍለ ጊዜው እንዲሁ እንዲባክን ያደርጋሉ፡፡ መምህራን በተሰጣቸው ክፍለ ጊዜ በሚገባ ማስተማራቸውን ለመከታተል የሚያግዙ አንዱ ስልት እያንዳንዱ መምህር የየዕለቱን ትምህርት ዕቅድ አዘጋጅቶ እየተጠቀመበት መሆኑን በማረጋገጥ ነው፡፡ የትምህርቱ አመራር እንደ አስፈላጊነቱ ክፍል ውስጥ በመግባት በዕቅዱ መሠረት መሄዱንና አለመሄዱን መፈተሽ ይችላል፡፡

በዐውዳችን ብዙ መምህራን በክፍለ ጊዜያቸው ትምህርቱን ከማስተማር በተጨማሪ የትምህርቱን ይዘት በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ያሳልፋሉ፡፡ ተማሪዎች ደግሞ ያንን በደብተራቸው ላይ ይገለብጣሉ/ይጽፋሉ፡፡ አንዳንድ የጽሑፍ ፍጥነት የሌላቸው ተማሪዎች ቶሎ ሳይገለብጡ በመቅረት በኋላ



ከጓደኞቻቸው ደብተር ተውሰው ይጨርሱታል፡፡ ለምሳሌ ያህል አንዳንድ መምህራን አንዱን ክፍለ ጊዜ ሲያስረዱ አንዱን ክፍለ ጊዜ ደግሞ ለተማሪዎቹ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ያሳልፋሉ፡፡ በእርግጥ በዐውዳችን መጻሕፍት በብዛት ስለማይገኙ ወይም ሁሉም ወላጆች የመግዛት አቅም ስለሌላቸው ወይም መምህራን ለተማሪዎች የሚሆነውን ማስታወሻ በኮምፒዩተር ጽፈው በማባዛት ለተማሪዎች ሁሉ መስጠት የሚችሉበት ዕድል በእኩል ደረጃ ስለማይኖር ይህን መንገድ መከተል የግድ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ ለትምህርት ሊውል የሚገባውን ሰዓት ይቀንሳል፡፡

መምህራን በትምህርት ክፍለ ጊዜያቸው የትምህርት ይዘቱን በማስተማር የሚያሳልፉ ሲሆን ተማሪዎች ብዙ እውቀትን ይጨብጣሉ፡፡ ተማሪዎች ከጥቁር ሰሌዳ ላይ መገልበጣቸው በራሱ የሚሰጣቸው ትምህርት የለም፤ ምናልባት የእጅ ጽሑፍ ይለማመዱበት ይሆናል፡፡ ወላጆች መምህራን ክፍለ ጊዜያቸውን ለትምህርት ብቻና በንቁ ማስተማር ላይ እንደሚያውሉ ለማወቅ ያስቸግራቸው ይሆናል፡፡ ሆኖም በዚያ ትምህርት ቤት የሚማሩትን ተማሪዎች በመጠየቅ ፍንጭ ማግኘት ይችላሉ፡፡ በእርግጥ የእያንዳንዱ መምህር ትጋትና የሕይወት ዲስፕሊን ስለሚለያይ የአንዱን ወይም የጥቂቱን መምህራን የክፍለ ጊዜ አጠቃቀም በመገምገም ስለ ትምህርቱ አጠቃላይ ድምዳሜ መስጠት ትክክል አይደለም፡፡ ወላጆች መገንዘብ ያለባቸው ቁልፍ ሐሳብ ትምህርት ቤቱ መምህራን ክፍለ ጊዜአቸው በንቁ ማስተማር ላይ ማዋላቸውን የሚከታተሉበት ስልትና ተሞክሮ አላቸው ወይ? የሚለው ነው፡፡

### 7. አመራሩ ከትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ ና ከወላጆች ጋር ምን ያህል ተቀናጅቶ ይሠራል?

የትምህርት ቤቱ ማሕበረሰብና ወላጆች ትምህርት ቤቱን «የእነ እገሌ ትምህርት ቤት» ወይስ «የእኛ ትምህርት ቤት» ነው የሚሉት? ብዙዎቹ የእኛ ትምህርት ቤት ብለው የሚጠሩ ከሆነ ትምህርት ቤቱ ተገቢውን ባለድርሻ አካላትን በንቃት የሚያሳትፍ ትምህርት ቤት ነው፡፡

የትምህርት ቤቱ ማሕበረሰብና ወላጆችም ጭምር የእኛ ትምህርት ቤት ነው ለማለት እንዲችሉ ትምህርት ቤቱ ሰፊ ሥራዎችን መሥራት ይኖርበታል፡፡ እያንዳንዱ የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማው ለማድረግ ቢያንስ እነዚህን ሦስት ነገሮች ማከናወን ይገባል፡-

*ተማሪዎችን በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ማሳተፍ፡-* ተማሪዎች ሐሳባቸውን ለመግለጽ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ዕድል የሚሰጣቸው ከሆነ ተማሪዎች ተሰሚነት እንዳላቸው ስለሚሰማቸው ለትምህርት ቤቱ ዕድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡ የእነርሱ ትምህርት ቤት ከሌሎች ትምህርት ቤቶች

መጥቆ እንዲገኝ ይጥራሉ:: ለትምህርት ቤቱ ንብረት፣ ስምና ዝና በበኩላቸው ይጠነቀቃሉ::

*ትምህርት ቤቱ ከወላጆች ጋር ተባብሮ መሥራት:-* ተማሪዎች በትምህርታቸው ስኬታማ እንዲሆኑ የመምህራን ብቃትና የተመቻቸ የመማር-ማስተማር ሂደት መኖር ብቻውን በቂ አይደለም:: ትምህርት ቤቱ ከወላጆች ጋር በቅርበት መሥራት አለበት:: ወላጆች የልጆቻቸው የመጀመሪያ መምህራን በመሆናቸው በሕይወታቸው ላይ ተጽዕኖ የማሳደር ኃይላቸው ከፍተኛ ነው:: ወላጆች ለልጆች ትምህርትና ጤናማ ዕድገት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ:: ሁለቱ በአጋርነት በሚገባ በሚሠሩበት ጊዜ ለልጆች የትምህርት ስኬት ሊኖሩ የሚችሉ ክፍተቶችን በመለየት መሙላት ይችላሉ:: ያለ ወላጆች ተሳትፎ አንድ ትምህርት ቤት ከሚያስበው ግብ መድረስ አይችልም:: ተማሪዎችም ትምህርት ቤቱና ወላጆች በአጋርነት እንደሚሠሩ ሲገነዘቡ ትምህርታቸውን በትጋት ይከታተላሉ::

### *ወላጆች ምን ማድረግ ይችላሉ?*

- ✓ በዕድሜያቸው ገና የሆኑ ልጆቻቸው የንባብ ክህሎታቸውን እንዲያገለብቱ መርዳት
- ✓ ልጆቻቸው የቤት ሥራ በሚሠሩበት ጊዜ ከጎናቸው በመሆን ሲጠይቁአቸው ማገዝ
- ✓ ልጆቻቸው ሁልጊዜ ከትምህርት ቤት እንዳይቀሩ መከታተል
- ✓ የልጆቻቸውን የትምህርት ውጤት መዝግቦ በመያዝ ተገቢውን ክትትል ማድረግ
- ✓ በትምህርት ቤት የወላጅ ስብሰባ ላይ በታማኝነት መገኘትና ንቁ ተሳትፎ ማድረግ
- ✓ አልፎ አልፎ ትምህርት ቤት የመጡ ከመምህራን ጋር ስለ ልጆቻቸው መነጋገር

ስኬታማ ትምህርት ቤት ወላጆችን ለማሳተፍ ከፍተኛ ጥረት ያደረጋል:: ወላጆች ልጆቻቸው ራሳቸውን በማይችሉበት ጊዜ ለልጆቻቸው የቅርብ መምህራን ናቸው፤ ነገር ግን የልጆቻቸው ዕድሜ እየጨመረ በሚሄድበት ጊዜ ኃላፊነታቸውን ለትምህርት ቤት በመስጠት ወደኋላ ገሸሽ ይላሉ:: ይህን በመረዳት ትምህርት ቤቱ ወላጆች በልጆች የትምህርት ሕይወት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያደርጋል::

*የመምህራንና የትምህርት ቤቱ አመራር በሰላም አብሮ መሥራት:* በመምህራንና በትምህርት ቤቱ አመራር መካከል መስማማትና መቻቻል በሚኖርበት ጊዜ መምህራን በትጋት ያስተምራሉ:: የመምህራን ፍልሰትም ይቀንሳል:: ግጭት በሚበዛበት ጊዜ ግን መምህራን ብዙውን ጊዜአቸውን ስለ ግጭቱ ስለሚያስቡ በትምህርት ላይ የሚኖራቸው ዝግጅትና ለማስተማርም የሚኖራቸው የልብ መነሳሳት ይቀንሳል:: ስለዚህ ወላጆች ለልጆቻቸው ትምህርት ቤት ሲመርጡ የትምህርት ቤቱ አመራር ከመምህራን፣



ከተማሪዎችና ከወላጆች ጋር አብሮ በሚሠራ ትምህርት ቤት ላይ ትኩረት ቢያደርጉ የተሻለ ነው::

## 8. አካባቢው ለትምህርት ምቹ ነው? ለትምህርት የሚያስፈልጉ መማሪያዎች አሉት?

ልጆች ትምህርታቸውን በሚገባ እንዲከታተሉ ምቹ አካባቢ መኖር አለበት:: ትምህርት ቤቱ ያለበት ሥፍራ ከጫጫታ የራቀና ሰላማዊ አካባቢ ከሆነ ልጆች አይረበሹም::

የማስተማሪያ ክፍሎች፣ ቤተ መጻሕፍት፣ የቤተ ሙከራ ማዕከሎች፣ የመዝናኛ ሥፍራዎች፣ የተማሪዎች የምሣ መመገቢያ አዳራሽ በአግባቡ መኖራቸውንና ምቹ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

በቅርብ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አንድ ትምህርት ቤት ለመጎብኘት ሂጄ ነበር:: ትምህርት ቤቱ በጣም ሰፊ ግቢ አለው:: የመማሪያ ክፍሎቹና ቤተ መጻሕፍቱ ጥሩ የሚባሉ ናቸው:: ነገር ግን ተማሪዎች የምሣ መመገቢያ ሥፍራ የላቸውም:: ምሣ ይዘው የመጡ ተመላላሽ ተማሪዎች በየቦታው ጥላ ሥር፣ ከክፍላቸው ውጭ በረንዳ ላይ ቁጭ ቁጭ ብለው ምሣቸውን ሲመገቡ አየሁ:: ከዚያም አንድ የሠፈር ልጅ አየሁና «ሁልጊዜ ምሣ የምትበሉት እዚህ ነው?» ብዬ ጠየኩት:: እርሱም «አዎን! የምሣ መብያ ሥፍራ የለንም» በማለት ከመለሰልኝ በኋላ ወደ ጨዋታው ሩጦ ሄደ::

መምህራን የፈጠራ ችሎታቸውን በመጠቀም የማስተማር ሂደቱን ለተማሪዎች አርኪ ለማድረግ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን መጠቀም ይፈልጋሉ:: አንዳንድ የማስተማሪያ ዘዴዎች ደግሞ የተለያዩ ቁሳ ቁሶችን ይጠይቃሉ:: መምህራን በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ለመማር ማስተማር ሂደት ስኬታማ መሆን የሚያግዙትን ነገሮች ለመፍጠር በሚደረገወ ጥረት የትምህርት ቤቱ አመራር አስፈላጊ ግብአቶችን በማቅረብ የሚተባበር ሲሆን የትምህርት ሂደቱ ስኬታማ ይሆናል::

የዘመናችን ቴክኖሎጂ በየጊዜው እየተሻሻለ ይሄዳል:: ባለፈው ዓመት የነበረው ነገር ዘንድሮ ተሻሽሎ ይመጣል:: ስኬታማ ትምህርት ቤት ዘመኑ ያፈራቸውን ቴክኖሎጂን ለመጠቀም ጥረት ያደርጋል:: ተማሪዎችም በየደረጃቸው ከቴክኖሎጂ ጋር ያስተዋውቃሉ:: በተለይ ተማሪዎች የተለያዩ ሙከራዎችን የሚሠሩባቸው ቤተ-ሙከራዎች ሲኖሩ ልጆች ከልጅነታቸው ጀምረው ሳይንሳዊ ሙከራዎችን ለማከናወን ዕድል ያገኛሉ:: ለቤተ-ሙከራዎች ቁሳቁሶችን ማሟላት ከፍተኛ የኢኮኖሚ አቅምን ቢጠየቅ አቅም

በፈቀደ መጠን ልጆችን በቀለም ትምህርት ብቻ ሳይሆን በተግባርም ለማስተማር ጥረት የሚያደርግ ትምህርት ቤት ይመረጣል፡፡

የመምህራንም የሥራ ጫና እንዲቀንስ ኮምፒዩተሮችን እንዲጠቀሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፡፡ መምህራን ትምህርቶቻቸውን በኮምፒዩተር መጻፍና ማስቀመጥ ከቻሉ በማንኛውም ጊዜ አባዝተው ለተማሪዎች መስጠት ከመቻላቸውም በላይ እንደ አስፈላጊነቱ ለማሻሻል ቀላል ይሆንላቸዋል፡፡ ስለዚህ ትምህርቱ ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር ለመሄድ ምን ያህል ጥረት እያደረገ እንደሆነ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

## 9. መምህራን በሚያስተምሩት ትምህርት ብቃት አላቸው ወይ?

የመምህራን ብቃት ባላቸው የትምህርት ደረጃ ብቻ አይለካም፡፡ የማስተማር ልምዳቸው፣ የሥራ ሚዘና ውጤታቸውና በየጊዜው በተማሩት የትምህርት መስክ ራሳቸውን ለማሻሻል የሚያደርጉት ጥረት ሁሉ በብቃታቸው ውስጥ ይካተታል፡፡

መምህራን ለማስተማር የተማሪዎቹን ልብ መያዝ አለባቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ የትምህርቱን ይዘት የተማሪዎችን አእምሮ በመያዝ ማስተላለፍ የሚችሉበትን ስልት መቀየስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ትምህርቱን በደንብ ማወቅ ብቻ ሳይሆን የማስተማር ዘዴውን በማወቅ በሚስብ መልክ ማቅረብ መቻል ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች የአንዳንዱ መምህር ክፍለ ጊዜ ማለቁን ሳያውቁ ያልቃል፡፡ የአንዳንዱ ደግሞ መምህሩን ገና ሲያዩት ፊታቸው ይጠቁራል፤ የግድ ስለሆነ ብቻ ክፍል ውስጥ ይቀመጣሉ፡፡ በዚያም ትምህርት የሚያመጡት ውጤት ዝቅተኛ የሆናል፡፡ አልፎ አልፎ ከመምህሩ የማስተማር ዘዴ ጥሩ አለመሆን የተነሣ ትምህርቱንም የሚጠሉ አይጠፉም፡፡

መምህራን የማስተማሩን ሥራ የማይወዱ ከሆነ በትጋት ለማስተማር ፍላጎት አይኖራቸውም፡፡ ሥራቸውን የሚወዱና የሚያከብሩ መምህራንን በክፍል ውስጥ ተማሪዎችም ይህን ይመሰክሩላቸዋል፡፡ በውስጥ ያለው ስሜት በተግባር ይታያል፡፡ ወላጆች በዚያ ትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ መምህራን ሥራቸውን የሚወዱ መሆናቸውን መደበኛ ባልሆነ መንገድ ከእነርሱ ጋር ግንኙነት በመፍጠር ማወቅ ይችላሉ፡፡ መምህራኑ በዚያ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት ሌላ አማራጭ የሥራ ዕድል በማጣታቸው እንደሆነ ፍንጭ የሚሰጡ ከሆነ ልጆችን ወደዚያ ትምህርት ቤት መላክ አይገባም፡፡



### ብቃት ያላቸው መምህራን ባሕርያት በጥቂቱ

- ✓ የሚያስተምሩትን የትምህርት ዐይነት በስፋትና በጥልቀት የሚያውቁ
- ✓ ስለማስተማር ዘዴዎች በቂ እውቀትና ክህሎት ያላቸው
- ✓ በትምህርት መስካቸው ያሉትን አዳዲስ የጥናት ውጤቶችን በመከታተል ራሳቸውን ከጊዜው ጋር የሚያራምዱ
- ✓ የሚያስተምሩትን ትምህርት በሚገባ ተዘጋጅተው ለማቅረብ በቂ ጊዜ የሚወስዱና የሚዘጋጁ
- ✓ የማስተማር ሙያቸውንና የሚያስተምሩአቸውን ተማሪዎቻቸውን የሚወዱና የሚያከብሩ
- ✓ የተማሪዎቻቸውን ሁኔታ (ፍላጎት፣ ተግዳሮቶች፣ የዕድገት ለውጦች) ለመረዳት ጥረት የሚያደርጉና ተገቢውን ምላሽ የሚሰጡ (ለምሳሌ አንድ ተማሪ የቤት ሥራ ሳይሠራ ቢመጣ ምክንያቱን በመጠየቅ ተገቢውን ምክር የሚሰጥ እንጂ ዝም ብሎ በዱላ የሚመታና የሚሳደብ ያልሆነ)
- ✓ ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁ የሚያበረታቱና ለጥያቄዎቻቸውም ተገቢውን ምላሽ የሚሰጡ፤ በወቅቱ መመለስ ካልቻሉ ደግሞ መጻሕፍትን አንብበ ለመመለስ ቃል የሚገቡና የሚተገብሩ
- ✓ አለመግባባትን በብስለት በመያዝ በትዕግሥት በመቻልና በጥበብ ለመፍታት የሚጥሩ የሚሉ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## 10. የቤተሰቤ የኢኮኖሚ አቅም ልጆቼን በዚያ ትምህርት ቤት ለማስተማር ያስችለኛል ወይ?

ወላጆች ልጆቻቸውን ማስተማር የሚፈልጉበት ፍላጎትና የኢኮኖሚ አቅማቸው ላይመጣጠን ይችላል፡፡ ወላጆች ለልጆቻቸው ትምህርት ቤት ሲመርጡ የኢኮኖሚ አቅማቸው ልጆቹን በዘላቂነት ማስተማር የሚችል መሆኑን መፈተሽ አለባቸው፡፡ አቅማቸውን ከግንዛቤ ውስጥ ሳያስገቡ ቀርተው ጥሩ የሚባልና ከፍተኛ ክፍያ የሚጠይቅ ትምህርት ቤት አስገብተው በኋላ ሲያቅታቸው ልጆቹን ከዚያ ከለመዱት ትምህርት ቤት አስወጥተው ሌላ ትምህርት ቤት ሲያስገቡ ልጆቹ በመሐል ይጎዳሉ፡፡

ወላጆች በአንድ በኩል እንደ ምንም ብለው የልጆቹን የትምህርት ቤት ክፍያ ችለው በሌላ በኩል ግን ሌሎች የልጆች መሠረታዊ ፍላጎት የማይሟሉ ሲሆን ልጆቹ ለችግር ይጋለጣሉ፡፡ በዚህ ጽሑፍ መጀመሪያ ላይ

እንደ ተጠቀሰው እንደ ዳንኤልና ሚስቱ ስለ ልጆች የትምህርት ቤት ክፍያ እየተጨነቁ መኖር በራሱ ችግር ነው። ከቀን ሥራ የሚገኘውን ገቢ ለትምህርት ቤት በመክፈልና እቤት ውስጥ ልጆች የሚበሉትን ምግብ ማጣታቸው ውሳኔያቸው ምን ያህል የኢኮኖሚ አቅማቸውን እንዳላገናዘበ ያሳያል። እቤት ውስጥ የሚበላ ነገር ኖሮም አንዳንድ ጊዜ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ካላቸው ቤተሰብ የተወለዱ ልጆች የሀብታም ልጆች የሚማሩበት ትምህርት ቤት ሲገቡ እንደ እነርሱ ለመኖር ካላቸው ምኞት የተነሣ ወላጆቻቸውን ያስጨንቃሉ። ወደ ትምህርት ቤት ይዞ የሚሄዱት ምሣ እንኳ ብዙ ጊዜ አንድ ዐይነት ሲሆን ምሣ ይዞ ላለመሄድ ወላጆቻቸውን ያስቸግራሉ። ስለዚህ ተጨንቀው ልጆችንም አላስፈላጊ የሥነ-ልቦና ውጥረት ውስጥ ላለማስገባት ከመጀመሪያው አቅምን ያገናዘበ ውሳኔ ማድረግ ይመረጣል።

በአብዛኛው በወላጅ አእምሮ ውስጥ ያለው የአንድ ትምህርት ቤት ክፍያ ከሌሎቹ ከፍ ያለ ከሆነ ያ ትምህርት በሚሰጠው ትምህርት ከሌሎቹ የተሻለ ነው የሚል አስተሳሰብ ነው። በክፍያውና በትምህርት ጥራቱ መካከል ግንኙነት እንዳለ ማሰብ ደግሞ ከዕለት ተዕለት ገጠመኝ የተገኘ ትምህርት እንደሆነ አስባለሁ። ምክንያቱም ገበያ ሄደን የአንድን ዕቃ ዋጋ በምንጠይቅበት ጊዜ ዋጋው ከፍ ያለ እንደሆነ ‹‹ዕቃው ጥራት ያለው ነው›› ብለን እናስባለን። ተመሳሳይ ዕቃ ከሌሎች ሥፍራዎች በአነስተኛ ዋጋ ብናገኝ እንኳ በልባችን ውስጥ ዋጋው ከፍ ላለው ዕቃ የምንሰጠው ግምት ከፍ ያለ ይሆናል። በተለያዩ ማስታወቂያዎች ‹‹ገንዘብ ሲገዛው የሚገባው ምርጥ ዕቃ›› የሚባለው በዋጋ ክፍያና በጥራት መካከል ግንኙነት እንዳለ ለማሳየት ነው። ወደ ትምህርት ቤትም ስንመጣ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳለ እናስተውላለን። አቅም አጥተው ቢተው እንኳ አንዳንድ ወላጆች ‹‹ገንዘብ ባገኝ ልጆቼን እዚያ ትምህርት ቤት አስገባቸው ነበር›› በማለት ክፍያው ከፍተኛ የሆነውን ትምህርት ቤት ለልጆቻቸው ሲመኙ ይደመጣሉ።

እንግዲህ ወላጆች ከላይ የተጠቀሱትን አሥር ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተገቢውን መልስ ካገኙላቸው ለልጆቻቸው ትምህርት ቤት ሲመርጡ ሚዛናዊ ውሳኔ ማድረግ እንደሚችሉ አምናለሁ። በመሠረተ ሐሳብ ልጆች በትምህርታቸው ስኬታማ እንዲሆኑ ከትምህርት ቤት አንጻር ሊኖሩ የሚገባቸው ትምህርት ቤቱ ብቃት ያለው አመራር መኖርና ከወላጆችና ከትምህርት ቤቱ ማሕበረሰብ ጋር በቅንጅት መሥራት፣ መምህራን ከተማሪዎች ጋር በደንብ ተቀራርበው እንዲሠሩ በክፍል ውስጥ ተገቢ ቁጥር ያለው ተማሪ መኖር፣ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በየጊዜው መከታተላቸው፣ ትምህርት ቤቱ ለተማሪዎች ሥነምግባር መታነጽ ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ፣ የትምህርት ቤቱ አካባቢ ለመማር



ማስተማር ሂደት ምቹ መሆኑ፣ ትምህርት ቤቱ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀሙ ለምርጫ የሚፈለጉ መረጃዎች ናቸው። እነዚህን መረጃዎች ካገኙ በኋላ ወላጆች ከራሳቸው የኢኮኖሚ አቅም ጋር በማነጻጸር መወሰን ይችላሉ። ወላጆች ለልጆቻቸው ያላቸውን ፍላጎትና የራሳቸውን አቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ቤተሰቡንና ልጆችን ለችግር የማያጋልጥ ውሳኔ ማድረግ ዘላቂ ጥቅም አለው።

## *ዋቢ መጻሕፍት*


Enlow, Robert C. & Ealy, Lenore T. Liberty *and Learning: Milton Firedman's Voucher Idea at Fifty.* CATO Institute, 2006.

Glasgow, Neal A. & Whitney, Paula J. *What Successful Schools Do To Involve Families: 55 partnership Strategies.* Corwin Press, 2009.

Gurrian, Michael, et al. *Boys and Girls Learn Differently: A Guide for Teachers and Parents.* 2001.

Poluha, Eva. *The Power of Continuity: Ethiopia through the eyes of its children.* The Nordic Africa Institute. Stockholm, 2004.

Rice, F. Philip. *Human Development: A Life Span Approach.* 2nd edition. NJ: Prentice Hall Inc., 1995 [pp. 218-219]